# <u>ሰባት ሲቀነስ ሰባት አስራ አራት!</u>

ሌዊ ሙሉጌታ

የሂሳብ ትምህርት እየከበዳቸው ካሉ ኢትዮጵያውያን ዛሬ ጎላ ብለው መታየት የጀመሩት የአንድ ድርጅት ጭፍን ደጋፊዎች ናቸው ቢባል በመጥፎ እንዳይወሰድ ከመጀመሪያውኑ አደራ ክብረ ነክ ወይ ዘለፋ አይለደም ማለትን እፈልጋለሁ፡፡ ወደ ዋናው ነጥቤ ከመግባቴ በፊትም ማንኛውም የፖለቲካ መሪ በሕዝብ ሆነ በመገናኛ ብዙሃን መተቸቱ የማይቀር ነው ወይም አለበት የሚለውን መርህ በመቃወም አንዳንዶች ገና ስልጣን ሳይዙ አፈና/እገዳ ያቀነቅናሉ ብዬ ማስጠንቀቅን እፈልጋለሁ፡፡ ይህ ደግሞ ተቀባይነት አይኖረውም፤ ሊኖረውም አይችልም፡፡ ከሂስ በላይ፤ ከትችት በላይ የሚሆን ሰው የለም፡፡ አለበለዚያማ መለስን አትንኩት፤ “ካርቱን” አትስሩበት፤አትቀልዱበት፤ አትተቹት የሚሉት ትክክል ናቸው ማለት ነው፡፡ ከዚያም አልፎ አንዱን የፖለቲካ መሪ እየተቸን ሌላውን ግን የሹም ዶሮ አድርጎ አትንኩት ማለት መሰረተ ቢስ ነው፡፡ ቢያንስ እኔ በግሌ መችም የምቀበለው ጩኸት አይደለም፡፡

ይህን ካልኩ ዘንዳ ግን ከዓመታት በፊት ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል መብራት ለተደረገመበት ለአዲስ አበባ ሕዝብ ምን ይመኙለታል ሲባሉ በሰጡት መልስ (በኤሌክትሪክ የሚንቀሳቀስ የትራም/ባቡር / መገናኛ ባሉት) የተነሳ አንድ ተቺ ሲቀልድ አንብቤ ደስ አለኝ እንጂ ቅርም አላለኝ ነበር ማለት እፈልጋለሁ፡፡ ክብረ ነክ መስሎም አልታየኝ፡፡ ገና ትግሉ ሳይጀምር ማንዴላ ማንዴላ-ጋንዲ ማለቱ ይደራና፤ ካባ ማልበሱ ይቀድምና አፋችን ይለጎማል፡፡ ቀደም ያን ክህደቱ የሚባለውን ሰው ለመተቸት የተነሱት (ዶክተር ታዬም ሳይቀር) ሲወገዙ ነበር፡፡ በአንፃሩ ግን የኢሕአፓ መሪ ዎች ቀን ተሌት በቀይ ሽብር ወንጀለኞችም ሆነ በስውርና ይፋ ወያኔዎች መተቸት ሳይሆን ሲሰደቡና ሲዘለፉ ዛሬ እሳቸው መህንዲሱ ተነኩ የሚሉቱ ምነዋ ሲሉ አልተደመጠም፡፡ ወደ ቁም ነገሩ ስንመለስ በመኢአድ ና ሌሎች (ተለጣፊ) ድርጅቶች ከወያኔ ጋር የተፈራረሙት የስነ ስርዓት ሰነድ አነጋጋሪ ሆኗል፡፡ የመኢአድ አባል ባልሆንም ይህ ድርጅት ይህን ሰነድ ከማፅደቁ በፊት ለአባላቱ ልኮ የተወያየበት አይመስልም፡፡ አባላቱ ድንገት “ ሰበር ዜና” የመጣባቸው መስለ ው የሚሰጡት የታማኝ አባል ማጠየቂያ እርሰ በርሱ የተጋጨ መሆኑ አልቀረም፡፡ አባላቱ ሰነዱን በሙሉ ልብ በይዘቱ ተነስተው ሊደግፉ ባለመቻላቸው በግድ ወደ ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ ክርክር መሄድ የተገደዱ መስሎኛል፡፡ በነገራችን ላይ መኢአድ እንደ ድርጅት ያመነበትን አቅዋም የመያዝ መብቱን ማንም ሊገፈው አይችልም፡፡ ኢዴፓም አየለ ጫሚሶም በየነም መረራ ም እንዲሁ፡፡ ድርጅቶች የሚወስዱትን አቅዋም ግን ትክክል ነው አይደለም ብሎ ሕዝብ መተቸ ት መቻሉን ማንም ሊገድብ አይችልም፡፡ ደፈራችሁን በሚልም ሊታገድ ወይ ሊተች አይገባም፡፡ በመሆኑም መኢአድ ከወያኔ ጋር ተፈራረመ የተባለውን ሰነድ በተመለከተ ዋና ዋና ጥያቄዎቹን ለማደበስብስ የተደረገውና እየተደረገ ያለው ጥረት ሁሉ ለሀገር ጠቃሚ አይደለም፡፡ የመኢአድ መሪ በውጭ ሀገር ያለውን ዜጋ በአሉታዊ መተቸት ትተው የፈረምነው ሰነድ ጠቀሜታው ይህ

ነው ብለው ማስረዳት አለባቸው:: ሌሎችም ሀላፊዎች እንዲሁ:: ጉዳዩን በተለመከተ ውይይቱ መሆን ያለበት --ማለትም ወያኔ ፓርላማ መግባት አለመግባት ይጠቅማል አይጠቅምም በሚል በ 1997 እንደተደረገው ሁሉ--

- የተፈረመው ሰነድ ከመጪው ምርጫ አንፃር የሕዝብን ጥያቄ ያንፀባርቃል፤ ያስከብራል ?
- የድርጅቶችን እጅ ያሰራል ወይስ አያስርም?
- መሰረታዊ ጥያቄዎች ባልተመለሱበት በስነ ስርዓት መፈራረሙ ጠቃሚ ነው ጎጂ?
- ተለጣፊዎችን ትቶ መኢአድ ይህን ሰነድ በመፈረም ሀገራዊ ግብን ያራምዳል ወይስ ለወያኔ ማጎብደድ ይሆንበታል?
- መሰረታዊ የሀገራችን ጥያቄዎች (ረሀብ፤ መሬት ለሱዳን መስጠቱ ለባዕዳን መሸጡ፤ መብት ረገጣና የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ መፈታት፤ የኑሮ ውድነት፤ወዘተ ) ተነስተዋል ወይስ ተረስተዋል? የሚሉት መመርመር አለባቸው::

ሰባት ሲቀነስ ሰባት አስራ አራት ያልኩበት ዋናው ምክንያት አንዳንድ ጭፍን ደጋፊዎች የወያኔ አገዛዝ የመኢአድን “ አስራ አራት ቅድመ ሁኔታዎች” ተቀብሏል ብለው በሀሰት ዜና ተመስርተው ሲከራከሩ በመስማቴ ነው:: ቅንጅት ስምንት ነጥቦችን አቀረበ ሲባል ነበር (በዚህም ላይ ብዙ ትችት ነበር) እንጂ 14 ጥያቄ መቅረቡን ቢያንስ እኔ አልሰማሁም:: ከዚያም እኔ እስከማውቀው ስምንቱ ሰባት ነጥብ ሆኑ ተብሎ ተነግሮ ነበር:: ይህ ሰባት ነጥብ በአሁኑ ድርድር ከቶም አልቀረበም ወይም የስምምነት መሰረት አልሆነም ( ፎርቹን ጋዜጣን ያነቧል):: ስለዚህ ሰባቱ ሳይነሳ ወይም ከሰባት ሰባት ተቀንሶ እያለ እንዴት 14 የሌለ ቅድመ ሁኔታ ተቀባይነትን አገኘ? ሰባት ሲቀነስ ከሰባት 14 መሆኑ ግራ ቢያጋባን አይፈረድብንም:: በአሁኑ ጊዜ የመሀንዲስ ኃይሉ ታማኝና የመጣ ቢመጣ ደጋፊዎች እየያዙት ያሉት አቅዋም ሁሉ አጠያያቂ ነው:: በመጠኑ ልጥቀሳቸው፤

- እንዴት አሳችውን ደፈራችሁ ለመተቸት!
- መኢአድ በኢትዮጵያ አንድነት ያምናል፤
- ለወያኔ ተቃራኒ አማራጭ ሀይል ለመሆን ይችላሉ
- ኢሕአፓና ሌሎች ናቸው ነገሩን ሁሉ የሚያበላሹት
- መኢአድ ቢፈራረም ሌሎችስ ተፈራርመው አልነበር?
- ሁሉንም ቅድመ ሁኔታ ወያኔ ተቀብሏል
- እስረኞቻችን ይፈታሉ ታያላችሁ
- ባይፈርሙስ ምን ሌላ አማራጭ አለ?
- እሳቸው ታማኝ ናቸውና በሚወስዱት አቅዋም ሁሉ መደገፍ አለባቸው
- ወዘተ ....

በቅሎ አባትህ ማን ቢሉት እናቴ ፈረስ ዓይነት መሰል እየመጣ ነው::መኢአድ ለኢትዮጵያ አንድነት ቆመ አልቆመ በክርክር አልገባም--የክህደቱም ኢዴፓ ሆነ በየነና መረራ ፀረ አንድነት አይደ

ሉም:: በእሳቸው በመህንዲሱ በጭፍኑ እመኑ ድግሞ ዜጋን መድፈርና መስደብም ነው:: በመርህ ና በአቅዋም እንጂ በግለሰብ ላይ እምነት የሚባል ነገር የለም--ሊኖርም አይገባም:: እሳቸው ተሳስተዋል ግን ያም ሆነ ይህ መደገፍ አለብን ብሎቅ መፈጠም ሀገርና ሕዝብን አለማስቀደምንና ለግለሰብ መገዛትን የሚያመለክት የተሳሳተና አሳፋሪም አቅዋም ነው:: ለወያኔ ተቃዋሚ አማራ ጭ ሀይል መሆን የሚቻለው በፀረ ወያኔ መርህና አቅዋም እንጂ ወያኔ ባዘጋጀው ድግስ ከበሮ በመደለቅ አይደለም:: ሌሎች በልዩ ልዩ ጊዜ ከወያኔ ከተፈራረሙ ወይም ሊፈራረሙ ከነበረ በሁ ኔታው መሰረት ሊተቹ  መገባቱ እንዳለ ሆኖ ዛሬ ግን መኢአድ ለተፈረራመው ሰነድ ማጠየቂያ ወይም ሽፋን ሊሆን አይችልም:: ወያኔ እንኳን ቀርቦ የማያውቅውንና የማናውቀውን 14 ቅድመ ሁኔታ ቀርቶ ቀርቦ የነበረውን ስምንቱንም ሰባቱንም አልተቀበለም:: ይህ ነው ሀቁ:: ሁሉም የፖለቲካ እስረኞችም አይፈቱም:: ለፖለቲካው ያመቸው ዘንድ ወያኔ ወይዘሪት ብርቱካንንና የተወሰኑትን ይፈታ ይሆናል:: በ 1997 የተያዙትን ሺዎችና ከዚያም በፊት የታገቱትን ግን ወያኔ አይፈታም:: እነዚህን ረሰተውና የተሰዉትንም ዘንግተው ከወያኔ መተቃቀፍን የሚደግፉ ሁሉ በክህደት መክሰሱ ይቅር ቢባል መከራ የተቀበሉትን አሳልፎ በመስጠት ቢከሰሱ አግባብ አለው:: ተቃዋሚዎች ባይፈርሙ ወይም በምርጫ አንካፈልም ቢሉ አማራጭ አላቸው-- ያለው አማራጭ ማዕቀብ ነው:: በምርጫ አለማሳተፍም የትግልና የታጋዮች ምርጫና አቅዋም ነውና:: በአጠቃላይ ይህ ሀገራዊ ወሳኝ ጉዳይ ከኢንጂነር ሀይሉ ማንነት ጋር ቅንጣትም ግንኙነት የለውም :: ጥሩ ሀገር ወዳድ ሆኑ ሆዳም ፖለቲከኛ ዋናው ጥያቄው ምን ሰነድ ተፈረመና የዚህም ይዘትና አንደምታ ምንድነው የሚለው ብቻ ነው:: እሳቸው በግል ባይፈልጉም በድርጅታቸው ታዘው መፈረም ይችላሉና ነው:: የተፈጠረውን ውዝግብ ሁሉ ደግሞ በኢሕአፓና ሌሎች ላይ ለመለጠፍ መሞከሩም እጅ እጅ ያለና ፍሬ ቢስ ሙከራ ነው:: የኢዴኃኅም የ1997 የድርድር ሙከራ ከዛሬ ው የተለየ ነው:: የበፊቱም የግዮኑ ጉባዔም ከዛሬው ጭራሽ አይገናኝም:: አሌ ከተባለም እነአበራ የማነአብ  ከደረሰባቸው ይማሯል:: ወያኔን በምርጫው በማጀብ ውጤት ይገኛል የሚለውን ቅዠት ሀቅ የሚሉ ካሉ  ከእንቅልፋቸው ይነቁ ዘንድ መምከር ተገቢ ነው::

ሀቅ ብዙዉን ጊዜ መራራ ሊሆን መቻሉ ይታወቃል:: ሀቁ ምንድነው?

- ወያኔ የምርጫ ህጉና ቦርዱን ይቆጣጠራል፤
- ወያኔ በምርጫ ተወዳዳሪዎች ነፃ ፉክክር ያደርጉ ዘንድ በሩን ዘግቷል፤
- የፖለቲካ እስረኞች እንደታፈኑ ናቸው፤ ስየል እየተፈፀመባቸው ነው፤
- የምርጫው ሂደት ሙሉ በሙሉ በወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር ነው፤
- ተቃዋሚ ነን ያሉት ድርጅቶች ራሳቸው በሰጡት መግለጫ  እንደተገለፀው ሁሉ ወያኔ የፈረመውን ሰነድ እንኳን እያከበረ አይደለም፤
- አልፈረምኩም ባዩ መድረክ ነገ ፈራሚ መሆኑ ቢታወቅም አብሮ አለመፈረሙ ለሁኔታው በጎ ገፅታን የሚሰጠው አይሆንም::
- ፈርመው ከወያኔ መተቃቀፋቸው ለትግሉ የሚሰጠው የሰናፍጭ ያክልም ጥቅም የለም::

- *የመኢአድ መሪ ሰነድ ፈርመው ስንቱን ዜጋ የገደለውን በደም የቀላ እጅ መጨበጠቻውን ደጋፊዎቻቸው በብልህነት ለማቅረብ የሚያደርጉት ጥረት በዜጎች ተቀባይነት አላገኘም፡፡*

የመለስ ቡድን ባልተቀየረበትና ሊሻሻልም ከቶም ፍንጭ በሌለበት ቆዩ ጠብቁ ጊዜ ስጡ ደግሞ የተጋለጠና የተነቃበት ማዘናጊያ ዘዴ ነው፡፡ ጊዜ ሰጪው " እንዴ !" ሊል ሲነሳ ድንኳኑ ተነቅሏል ፣ የፈራኸው ደርሷል ይሆናል፡፡ " ሶሪ--እናዝናለን፣ ሌላ ጊዜ " ምላሽ ይሰጠውና ቁጭቱን አቅፎ ይሰቃያል፡፡ የ 1997ኡን በ2002 ልንደግም ነውና ተኛልን ብሎ ሕዝብን መጥራቱ አያሳፍርም? ዛሬ ወያኔን የሚገረስስ ሀይል የለምና ዛሬ ለወያኔ መጋዣ ሆንን እንጫን ማለት ደግሞ ውርደት እንጂ ብልጠት አይደለም፡፡ በመሆኑም ከወያኔ የተፈራረሙት የመኢአድ መሪዎችና ደጋፊዎች

- በውጭ ባለው ዜጋ ላይ ዘመቻን ትተው
- የራሳቸውን ችግር በሌሎች ድርጅቶች ላይ መጫኑን ትተው
- ሰባት ሲቀነስ ሰባት አስራ አራት ሆነ ተዓምር ማለቱን ትተው

ለሕዝብም፣ ለአባሎቻቸውም ለደጋፊዎችም ሁሉ ለምን ሰነዱን እንደፈረሙና እንዴትስ ለሕዝብ ትግልና ለሀገር ይህ እርምጃቸው እንደሚጠቅም ማስረዳትና ማሳመን (ከቻሉ) ይጠቅባቸዋል፡፡ ሌላው ሁሉ ልፈፋ ሰይጣን ለዓመሉ መፅሀፍ ቅዱስ ይጠቅሳል ሆኖ ራሳቸውን ያጋልጣቸዋል፡፡